# የታክሲዎች ስራ ማቆም አድማ እንድምታ

እስክንድር ነጋ

አዲስ አበባ

አስኮ ፣ ሳፍቶ፣ ለቡ፣ አያት፣ ሲ.ኤም.ሲ፣ ዓለም ባንክ፣ ቀራኒዮ፣ ኮተቤ ፣ ቃሊቲ ... የማለዳ ታክሲ ለወትሮውም መከራ ነው። ግፊያው የደብድብ ያህል ነው። ትላንት ሰኞ ግንቦት 8/2003 ግን፣ ተጋፍቶ የሚገባበት ታክሲ የጠፋው ገና ከጠዋቱ 12 ሰዓት ጀምሮ ነበር። የአንድ ሰዓቱን ግፊያ እየሸሸ ቀደም ብሎ ከቤቱ የሚወጣው የከተማዋ ነዋሪ ታክሲዎች የምር አድማ መተዋል ብሎ መጠርጠር የጀመረው የወትሮ ደንበኞቹ የውሀ ሽታ ሆነው ሲቀሩበት ነበር። የቻለ እንደ ሰርዲን በሚጠቀጠቁት አውቶብሶች ላይ እንደምንም ተሸጉጦ አመለጠ። ከፊሉ በእግሩ አስነካው። እድለኛው የቤት መኪና እየተባበረው በምቾት ወደ መሀል ከተማ ዘለቀ። ብዙዎች ከስራና ከትምህርታቸው ቀርተው ወደቤታቸው ተመለሱ።

የሚገርመው፣ በተፈጠረው እንግልት ያዘነና የተቆጣ እምብዛም መሆኑ ነበር።ለወትሮው፣ የአዲስ አበባ ነዋሪና ታክሲዎች ብዙም አይፋቀሩም። ህዝቡ ታክሲዎችን ያማርራል። ታክሲዎች ህዝቡን ያማርራሉ። ተቻችለው የሚኖሩት የግድ ነው። በዚህች እለት ግን የታክሲ ሹፌሮቹ ህብረት የህዝቡን ልብ አሸንፏል።

ይሄ ሕዝብ መተባበር የጠማው ሕዝብ ነው። ከቀይ ሽብር በኋላ በምርጫ 97 ለአጭር ጊዜ ብልጭ ብሎ ድርግም ብሎበታል። መከዳዳት፣ መጠላለፍ፣ መሰባበቅ፣ መወነጃጀል፣ መራራቅ፣ እንደሬት የመረረው ሕዝብ ነው። እንደ ቱንዚያ፣ እንደ ግብፅ፣ እንደ ሶሪያ፣ እንደየመን ሚሊዮኖች በአንድ ሳምባ ለመተንፈስ የጓጓ ሕዝብ ነው። ከምንም በላይ ሕዝቡ በታክሲዎቹ ህብረት ተደስቷል።

በዛ ላይ፣ ከታክሲዎቹ ጥያቄ በስተጀርባ ያለውን እውነታ ሕዝቡ የሚጋራው ነው። ጣሪያ በነካው የዋጋ ግሽበት ያልተደቆሰ የሕብረተሰብ ክፍል የለም። ሕዝቡ መኖር እያቃተው ነው። በሽሮ እንኳን መኖር ከብዷል።

የታክሲዎች ገቢ ባለበት ከቆመ ሁለት አስር አመታት ተቆጥረዋል። ኢህአዴግ በ1983 ስልጣን ሲይዝ የታክሲዎች የእለት ገቢ ከ100 እስከ 120 ብር ነበር። ከሃያ ዓመታት በኋላ ዛሬም ያው ነው። የቤንዚን ዋጋ ግን በሌትር ከሁለት ብር ወደ ሃያ ብር ተሰቅሏል። የሹፌሮቹም ገቢ ባለበት እንደቆመ ነው።

የታክሲ ስራ ሩጫ ነው። አድካሚም ነው። ነፃነትንም የሚሻ ነው። ወደ አንድ አቅጣጫ ተሳፋሪ ይዞ ሄዶ ተመላሽ ከጠፋ፣ ኪሳራ ነው። የታክሲ ሹፌር ከመሬት ተነስቶ የሚወደውና የሚጠላው ሰፈር የለም። ስራ ካለ ይሄድበታል። ስራ ከሌለ የሚሄድበት ምክንያት የለም። እንዲያወጣው ሲሄድም ሲመለስም ተሳፋሪ መሙላት አለበት። ከቤንዚኑ ውድነት አኳያ በከፊል እየሞላ መመላለስ አያዋጣም። ስለዚህም

፣የታክሲን አቅጣጫ የሚወስነው ገበያው ነው፤ ሹፌሩ ወይም ባለቤቱ አይደለም። ኢህአዴግ ግን አሁን እኔ ልወስን እያለ ነው። ገበያው ስላልሰራ መንግሥት ጣልቃ መግባት አለበት ባይ ነው።

ኢህአዴግ ገበያው ችግር እንዳልበት ሲናገር የመጀመሪያው አይደለም። የሙዝ ፣ የስኳር፣ የስጋ፣ የዘይት ዋጋዎችንም አስተካክላለሁ ብሎ ከተነሳ ሰነባብቷል። ውጤቱ ግን አልሰመረም። ሸቀጦቹ ከገበያ ጠፍተዋል። የስኳርና የዘይት ግዢ ሰልፎች የአዲስ አበባ መለያዎች እየሆኑነው። የዋጋ ግሽበቱ ደግሞ ጭራሽ ተባብሶ 30 ከመቶ ደርሷል። በሌላ አነጋገር ፣ መንግስት እታች ድረስ ወርዶ ሲቆጣጠር ውጤቱ የተበላሸ ነው የሚሆነው። በሸቀጦቹ ዙሪያ የተፈጠረው ችግር ወደታክሲዎቹ ላለመሄድ ታኮ ሊሆን ይገባ ነበር።

ባለታክሲዎቹም ሆኑ የታክሲ ሹፌሮች የስምሪት ህጉ ተግባራዊ ከመሆኑ በፊት እንደማያወጣቸው ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ አበክረው ተናግረዋል። ኢህአዴግ ግን የሚናገርበት እንጂ የሚያዳምጥበት ጆሮ የለውም። ሰሚ አላገኙም። ወደስራ ማቆም የሄዱት ተገደው ነው። ምርጫ አልነበራቸውም።

ኢህአዴግ ለሥራ ማቆሙ ምላሽ የአዲሱ ዘመን ማብሰሪያ ሆኗል። የወትሮው ፉከራ፣ ሸለላ፣ ማስፈራራት፣ ድብደባና እስር አልተተገበሩም። ድምፁን ማጥፋት ነው የመረጠው። ወደ ክፍለ ሀገር የሚወጡ ሚኒባሶችና አውቶብሶች ክፍተቱን እንዲሞሉ ጥሯል። የደጋፊዎቹ ታክሲዎች ወጥረው ሰርተዋል። ከነበረው እጥረት አኳያ ግን፣ ክፍተቱ አልተሞላም።

ሰኞ ረፋዱ ላይ ስምሪቱ እንዲቆምና ታክሲዎች እንደልብ ተንቀሣቅሰው እንዲሰሩ የቃል መመሪያ ተሰጥቷቸዋል። በዚህ የተደሰቱ በርካታ ታክሲዎች አመሻሹ ላይ ወጥተዋል።

ዛሬ ማክሰኞ ታክሲዎች በብዛት አሉ። የሚሰሩት ግን በተሰጣቸው መስመር ብቻ አይደለም ። አንዳንዶቹ እንደፈለጉ ይሰራሉ ። የሚናገራቸው የለም። መጨረሻው አይታወቅም።

የስራ ማቆሙ አድማ ተሳካም አልተሣካም ግን ፣ ቢያንስ ቢያንስ ህዝብ መተባበር እንደሚችል አሳይቶናል። ይህ ታላቅ ቁም ነገር ነው። በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ ፣ የኢህአዴግ እብሪት መተንፈሱ ታውቆበታል። ይህ ደግሞ ፣ ለኢህአዴግም ፣ ለህዝብም፣ ለሀገርም የሚበጅ ነው።